# የአቶ ዐቢይ መግለጫና ማስጠንቀቂያ በተጠየቅ ሲፈተሽ!!!

አቶ ዐቢይ በመግለጫቸው "የጋራ የሽግግር መንግሥት ይመሥረት!" የሚሉ ተቃዋሚዎችን "የሥልጣን ጥመኞች!" በማለት እንዲያርፉ በብርቱ አስጠንቅቀዋል፡፡ አንዳንድ ተቃዋሚዎች እየገለጹ እንዳሉትም ማስጠንቀቂያው ወደተግባር ተቀይሮ ክትትል እየተደረገባቸውና ዛቻ ማስፈራሪያ እየተሰነዘረባቸው ነው!!!

እኔ የምለው ወያኔ/ኢሕአዴግ ወይም ብልጽግና ሥልጣኑ የተሰጠው ሳይፈልግ በግድ "ግዛ!" ተብሎ ተጭኖበት ነው እንዴ??? የኢትዮጵያን ሕዝብ ለሠላሳ ዓመታት ፍዳውንና ቁምስቅሉን እያሳየና እየፈጀ፣ ምርጫ እያጭበረበረና እየገለበጠ "ሥልጣን ወይም ሞት!" ብሎ ሙጥኝ ያለ አገዛዝ በምን ሞራሉ ነው ሥልጣን ይዘው የማያውቁ ተቃዋሚዎችን "የሥልጣን ጥመኞች!" ብሎ ለመዝለፍና ለማውገዝ የሚበቃው በሞቴ??? ወይ እፍረት ማጣት እናንተየ!!!

አቶ ዐቢይ በመግለጫቸው በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት በተዛባው የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ የመፍትሔ ሐሳብ ሰነዘሩ ያሏቸውን ወገኖች በሦስት በመክፈል፦

1ኛ. ሕጋዊ ወይም ሕገመንግሥታዊ መፍትሔ እንደሚያስፈልግ የሚያቀርቡ ነገር ግን ከሕገመንግሥት ትርጉም ውጭ ያሉ ሕገመንግሥታዊ አማራጮችን የሚያቀርቡ፣

2ኛ. ሕገመንግሥታዊ ትርጉም የተሻለ አማራጭ መሆኑን የሚያቀርቡ፣

3ኛ. በሕጋዊ አኪያሔድ ሳይሆን በፖለቲካ መፍትሔ የሚፈታ ነው የሚሉ፡፡ ለዚህም በሽግግር መንግሥት መቋቋም ወይም ተፎካካሪ ፓርቲዎችን ያቀፈ መንግሥት መፍትሔ ነው የሚሉ ናቸው፡፡

በማለት ሆን ብለው ባልደራስ ያቀረበውን ከሦስቱ የተለየውንና "ለሰላም፣ ለፍትሕ፣ ለዲሞክራሲ ቆሚያለሁ!" የሚል ማንኛውንም አካል ሁሉ ሊያስማማ የሚችለውን ወይም በምንም ተአምር ቢሆን ውድቅ ሊያደርገው ወይም "አልቀበልም!" ሊለው የማይችለውን ማለትም በጠላትነት የሚፈላለጉ ፓርቲዎችን፣ የሚቃረኑ ዓላማዎችና ግቦች ያላቸውን ፓርቲዎችን፣ በቁጥር በርካታ የሆኑ ፓርቲዎችን አነስተኛ ቁጥር ያለውን የመንግሥት ካቢኔን አስማምቶ ማከፋፈልና ተግባብቶ፣ ተማምኖ፣ ተናቦና ተስማምቶ የሚሠራ መንግሥትን መፍጠር ፈጽሞ የማይቻልና ሀገርንም ወደ ቀውስ የሚከት አደገኛ ሐሳብ በመሆኑ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባልነትና ወገንተኝነት እንዲሁም ከጎሳ ወገንተኝነት (ጎሰኝነት) ነጻ በሆኑ ምሁራን ተመሥርቶ ምርጫ እስኪደረግና በሕዝብ የተመረጠው መንግሥት ሥልጣኑን እስኪረከብ ድረስ የሚቆይ የሽግግር ወይም የባለአደራ መንግሥት የማቋቋምን አማካኝ፣ ፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊ የመፍትሔ ሐሳብን ግን ሆን ብለው ዘለውታል!!!

አቶ ዐቢይ ይሄንን የመፍትሔ ሐሳብ ሆን ብለው ለመዝለል ወይም የመፍትሔ ሐሳቡ እንዳልቀረበ በመቁጠር ዓይቶ እንዳላየ ሰምቶ እንዳልሰማ ለማለፍ የተገደደው ሐሳቡን ውድቅ ለማድረግ ሊያቀርበው የሚችለው ምንም ዓይነት ምክንያት ስለሌለ ነው!!! ይሄ ለአቶ ዐቢይና ለአገዛዙ ታላቅ ሽንፈት ነው!!!

የሚገርመው አቶ ዐቢይ ብቻ አይደለም ይሔንን የመፍትሔ ሐሳብ እያፈኑት ያሉት፡፡ የአገዛዙን የብዙኃን መገናኛዎችን ጨምሮ "ነጻ ሚዲያ ነን!" የሚሉ የአገዛዙ ደጋፊዎችና በውስጣቸው የሚሠሩ ጋዜጠኞች፣ በእንግድነት የሚያቀርቧቸው ተንታኞችና ፖለቲከኞች ሁሉ የጋራ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም የጠየቁ ተቃዋሚዎችን ሐሳብ ብቻ በማንሣት በአሉታዊ መልኩ ይተቻሉ እንጅ ባልደራስ ያቀረበውን ማዕከላዊና አዋጭ አማራጭ የመፍትሔ ሐሳብ ፈጽሞ ማንሣትና ሽፋን መስጠት ሳይፈልጉ ሆን ብለው እያፈኑት ይገኛሉ!!!

ይመስለኛል ሐሳቡ ገዥ ወይም አሸናፊ ሐሳብ በመሆኑ "ሕዝብ ይደግፈዋል!" በሚል ሥጋት ነው አፈና እያደረጉበት ያሉት፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! እንደምንም ብለህ ይሄ አማራጭ የመፍትሔ ሐሳብ እንዲወሰድ ወይም በሥራ ላይ እንዲውል ወይም እንዲመረጥ ማድረግ ካልቻልክ ያልቅልሃል!!! ይሄ ባልደራስ ያቀረበውን የመፍትሔ ሐሳብ ያቀረብኩት እኔ መሆኔ ይታወቃል!!!

አቶ ዐቢይ በመግለጫቸው ጨምረውም ተቃዋሚዎችን ሲከሱ "ሕገመንግሥቱ ምርጫን ስለማራዘም የደነገገው ነገር የለውም እያሉ እየተቃወሙ በሌላ በኩል ግን በሕገመንግሥቱ ያልተደነገገ ወይም ሕገመንግሥቱ ሥልጣን መያዣ መንገድ ነው ብሎ ካስቀመጠው የምርጫ ሥርዓት ውጭ የጋራ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም ይላሉ!" በማለት ለማሸሚጠጥ ሞክረዋል!!!

አቶ ዐቢይ ሆይ! ሕገመንግሥትዎ ያላለ እንደሆነ ታዲያ ሀገሪቱ ያለ መንግሥት ትቅር ወይ??? የእርስዎ አገዛዝ የሥልጣን ዘመን መቸ እንደሚጠናቀቅ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ "ከዚያ በኋላ ያለ መንግሥት ቅሩ!" ነው ወይ የሚሉት??? ሕገመንግሥታቹህ መፍትሔ ባለማስቀመጡ እኮነው በሌላ መንገድ መፍትሔ ለማምጣት የተገደድነው???

በሌላ በኩልም ሀገሪቱ ከዚህ ሕገመንግሥት ተብያቹህ በፊትም የነበረችና ፈጣሪዋ ይሄ ሕገመንግሥት ተብያቹህ ስላልሆነ ነው ሕገመንግሥታቹህ ባይልም እንኳ ሀገሪቱ ያለ መንግሥት መቀመጥ ስለሌለባት በዚህ መንገድ ከሕገመንግሥታቹህ ውጭ መፍትሔ ማምጣት ግድ የሚሆንብን፡፡ ግልጽ ነው አቶ ዐቢይ???

አቶ ዐቢይ ሕገመንግሥትዎ የእርስዎና የአገዛዝዎ ሥልጣን መቸ እንደሚያበቃ ጥርት አድርጎ አስቀምጧል፡፡ ሥልጣን ላይ ያለ መንግሥት የሥልጣን ዘመኑ ሲጠናቀቅ እንዲህ ባለ አጋጣሚ ምርጫ ማድረግ ባይቻል ምን መደረግ እንዳለበት ግን ምንም የሚለው ነገር የለውም፡፡ አርቆና አስፍቶ የማሰብ ችግር አለበት፡፡ እና እሱ ምንም ያላለ እንደሆነ ምንም አላለምና ብለን ያለ መንግሥት መቅረት አለብን ነው ወይ የሚሉት አቶ ዐቢይ???

ነው ወይስ እርስዎና አገዛዝዎ የገዛ ሕገመንግሥታቹህን በሚፃረር ወይም በሚጥስ መልኩ እያደረጉ እንዳሉት ሕገመንግሥትዎ ሥልጣን መያዝና በጊዜ ለተገደበው የአምስት ዓመት የሥልጣን ዘመን ብቻ ሥልጣን ይዞ መቆየት የሚቻለው በምርጫ ብቻ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ተናግሮ እያለ በሕገመንግሥታዊ ትርጉም ስም ሕገመንግሥቱ ጨርሶ ያላለውንና ያላሰበውን በማስባል በውንብድና ሥልጣንን ማራዘሙ ነው ትክክሉና ሞራላዊው ታዲያ???

በዚህ መልኩ ሕገመንግሥቱ ጨርሶ ያላለውንና ያላሰበውን ነገር "ብሏል!" በማለት ሕገወጥ የቡድን ፍላጎትን ማሳካት ከተቻለማ መንግሥታት ያለ ሕገመንግሥት እንደፈለጉ በመሰላቸው መንገድ ያሥተዳድራሉ እንጅ ሕገመንግሥት መጻፉ ወይም መደንገጉ ለምን አስፈለገ ታዲያ አቶ ዐቢይ???

ሕገመንግሥት የመንግሥትን ሥልጣን ለመገደብ አይደለም ወይ የሚጻፈው ወይም የሚደነገገው??? ሌላ ምንድን ነው ፋይዳው??? መንግሥታት ማጣፊያው ባጠራቸው ቁጥር "በጊዜው ስላልታሰበ ነው እንጅ እንዲህ መባሉ አይቀርም ነበረ!" እያሉ ከተጻፈው ወይም ከተደነገገው ውጭ ሁኔታውን ለራሳቸው እንዲመች የማድረግ ሥልጣንና መብት ካላቸውማ ምኑን ሥልጣናቸው ተገደበ??? ሕገመንግሥት የመጻፉስ ፋይዳ ምን ሊሆን ነው ታዲያ??? እንኳንና ባለድርሻ አካላትና ሕዝቡ እየተቃወመ ባይቃወሙ እንኳ እንዲህ ዓይነቱ ድፍረት ፈጽሞ ተገቢ አይደለም!!! በሕገመንግሥቱ ያልተደነገገ እንዲህ ያለ ነገር ሲያጋጥም በጉዳዩ ላይ የመወሰን ሙሉ መብትና በጊዜ ገደብ የማይወሰን ሥልጣን ያለው የሀገሪቱ ሕዝብ ነው እንጅ በሕገመንግሥቱ ሥልጣን ያልተሰጠውና ሥልጣኑ በጊዜ የተገደበው አገዛዝ አይደለም!!! በየትኛውም አመክንዮ ቢታይ ይሄ ፈጽሞ ትክክል አይደለም!!! የለየለት ሕገወጥነትና አንባገነንነት ነው!!!

"ሕዝብ ይወስንበታል!" የሚለው አሠራር አሁን በወረርሽኝ ምክንያት እንዳጋጠመን የማይመች ቢሆን እንኳ ለጊዜው ለሁሉም ፓርቲዎች አማካኝ የሆነ ወይም ሕዝብን ተጠቃሚ የሚያደርግ፣ የሕዝብን መብትና ሥልጣን የማይጋፋ የመፍትሔ አማራጭ ተፈልጎ ይታለፍና ባመቸ ጊዜ ግን በሕዝብ ድምፅና ውሳኔ ጸድቆ የሕገመንግሥቱ ድንጋጌ አካል ይደረጋል እንጅ በሌለና ባልተሰጠ ሥልጣን በማንአለብኝነትና በጉልበት ያልተደነገገን ነገር ለቡድን በሚመች መልኩ እንደተደነገገ አድርጎ እራስን ተጠቃሚ ለማድረግ መጣር የለየለት ውንብድና እንጅ ፈጽሞ ሕጋዊ አኪያሔድ አይደለም!!!

ይሄ ከላይ ያልኩት ትክክለኛ አኪያሔድ የሚሠራውም ሕገመንግሥታቸው በሕዝብ ነጻ ተሳትፎ፣ ይሁንታና ስምምነት ለተደነገጉ ሕገመንግሥቶች ነው፡፡ በእኛ ሀገር ሁኔታ ግን ይሄ ሕገመንግሥት የሚሉት የወያኔና የኦነግ የጥፋት ሰነድ እንጅ በኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻ ተሳትፎ፣ ይሁንታና ስምምነት የተደነገገ ስላልሆነ "ሕዝብ ይወስን!" ወደሚል ነገር ከተገባ ጉዳዩ በአጠቃላይ ሕገመንግሥት ተብየው እንደገና መታየት ይኖርበታል እንጅ በአንድ አንቀጽ ብቻ የሚወሰን አይደለም!!!

ባጠቃላይ በተለይም "የሕግ ባለሙያ ነን!" የምትሉ ያለ ሆዳቹህ ሌላ ምንም የማይታያቹህ ሕሊናቢስ የአገዛዙ ምንደኞች ታሪካዊ ስሕተት እንዳትፈጽሙ ተጠንቀቁ!!! "ለሕግ የበላይነት፣ ለፍትሕና እኩልነት ቆሜያለሁ፣ ተጠያቂነትና ኃላፊነት ይሰማኛል፣ ጥብቅናየ ለቡድን ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለሀገር ነው፣ ለሞያዊ ሥነምግባሬ ተገዥና ታማኝ ነኝ!" የሚል የሕግ ባለሙያ በምንም ተአምር ቢሆን አገዛዙ እያለው ባለው መልኩ ሊያስብና ሊሠራ አይችልም!!! ተሳስታቹህ እንደ ከፍሌ ወዳጆ ተረኛ የታሪክ ተወቃሽና ተከሳሽ እንዳትሆኑ ብትጠነቀቁ ይሻላል!!!

እዚህ ላይ መግለጥ የምፈልገው የአገዛዙ ቁማር አለ ልብ ብላቹህ ስሙኝ፡፡ ወያኔ እንደምታዩት ሁሉን አቀፍ የጋራ የሽግግር መንግሥት የመፍትሔ አማራጭ ደጋፊና አቀንቃኝ ሆኖ ቀርቧል፡፡ እውነት እንዳይመስላቹህ ቁማር ነው፡፡ ለውጥ በሚባለው የወያኔ/ኢሕአዴግ ድራማ የለውጥ ተዋናይ ሆነው እየተወኑ ያሉት የኢሕአዴግ አባላት ወይም ብልጽግናዎች " ሁሉን አቀፍ የጋራ የሽግግር መንግሥት የመፍትሔ አማራጭ

ነው!" የሚሉትን ተቃዋሚዎች የለውጥ እንቅፋት ሆነው እየተወኑ ካሉት የኢሕአዴግ አባላት (ወያኔ) አጫፋሪዎች አስመስሎ ለመምታት እንዲያመችና አማራጩ ተቀባይነት እንዳይኖረው ለማድረግ የተሴረ ሴራ ነው እንጅ ወያኔን በባሕርይው እንደምታውቁት ፈጽሞ ሁሉን አቀፍ የጋራ የሽግግር መንግሥት የመፍትሔ አማራጭ ደጋፊ አይደለም፡፡ ይሄ አማራጭም ወያኔን ተጠቃሚ የሚያደርግ አይደለም!!!

አዎ መግቢያየ አካባቢ በገለጽኩት ምክንያት ሁሉን አቀፍ የጋራ የሽግግር መንግሥት የመፍትሔ አማራጭ የሚለው አማራጭ ፈጽሞ ሊሆን የማይችል፣ የማይጠቅምና አደገኛም ነው፡፡ ተቃዋሚዎች ብልጥና አስተዋይ ከሆኑ አገዛዙ ይሄንን ካርድ የፖለቲካ ቁማሩ መጫወቻ በማድረግ የራሱን ጥቅም እንዳያስጠብቅበትም ከፈለጉ ባልደራስ ያቀረበውን ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባልነትና ወገንተኝነት እንዲሁም ከጎሳ ወገንተኝነት (ጎሰኝነት) ነጻ በሆኑ ምሁራን ተመሥርቶ ምርጫ እስኪደረግና በሕዝብ የተመረጠው መንግሥት ሥልጣኑን እስኪረከብ ድረስ የሚቆይ የሽግግር ወይም የባለአደራ መንግሥት የማቋቋምን አማካኝ፣ ፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊ አማራጭ የመፍትሔ ሐሳብን ደግፈው ይቁሙ!!! ሴረኛውን፣ ሸፍጠኛውን፣ ቁማርተኛውን ወያኔ/ኢሕአዴግን ድባቅ መምቻ መሣሪያው ይሄ ብቻ ነው ተቃዋሚዎች ንቁ አድርጉትም!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው